# <u>የታላቁ ዐውደ ዓመት በዓል</u>
# <u>ምንባባትና መዝሙራት።</u>

መስከረም አንድ ቀን፡ በርእሰ ዓውደ ዓመት፥
በድንግል ማርያም፡ በእናቲቱ ልደት፥
በኢየሱስ ክርስቶስ፡ ባምላክ ልጇም ትስብእት፥
የተወረሰውን ዓመተ ምሕረት፥
በአዳምና ሔዋን፥ የዓለሙን ፍጥረት፥
በቅዱሱ ኪዳን፡ የኢትዮጵያን ነጻነት፥
የተላበሱባት፡ በእግዚአብሔርዋ መንግሥት፥
የኢትዮጵያ ሰዎች፥ ደግሞም ኢትዮጵያውያት፥
ባሉበት ቦታና በኑሮአቸው ዓይነት፥
በግል፥ በቤተሰብ፥ በኅብረሰብነት፥
ቤተ ክርስቲያናቸው፡ መካነ ኪዳናት፥
በቅዱሱ መንፈስ፡ በተሰበሰቡበት፥
የመስቀል ማኅተም፡ ኾኗቸው አብነት፥
በ፬ቱ ማዕዝናት በሚፈጸም ሥርዓት፥
በታላቁ በዓል፡ ግጻዌው ወጥቶለት፥
ይኸው ያቅርቡበት፡ የምስጋናን መሥዋዕት::

---

## ፩ኛ፡ በምዕራቡ ማዕዘን፤
## <u>ስለፍጥረት ልደትና ርእሰ ዓውደ ዓመተ ምሕረት፤</u>

ምንባብ፡- ሮሜ ምዕ. ፲፫፥ ቁ. ፰-፲፬፤
ራእ. ምዕ. ፳፩፥ ቁ. ፩-፰፤
ሐዋ. ምዕ. ፫፥ ቁ. ፲፱-፳፯::

ምስባክ፡- መዝ. ፷፬፥ ቁ. ፲፩-፲፪፤

ወትባርክ፡ አክሊለ ዓመተ ምሕረትከ፤ — የምሕረትህን ርእሰ ዓውደ ዓመት፡ ትባርካለህ፤
ወይጸግቡ፡ ጠላተ ገዳም፤ — ምድረ በዳው፡ በልምላሜ ይሸፈናል፤
ወይረውዩ፡ አድባረ በድው:: — የበረሃ ተራሮች፡ በዝናብ ይረካሉ::

ወንጌል፡- ሉቃ. ምዕ. ፬፥ ቁ. ፲፬-፳፱::

## ፯ኛ፡ በሰሜኑ ማዕዘን፤

# ስለቅዱሱ ኪዳኗ ኢትዮጵያ ልደትና ነጻነት፤

ምንባብ፡-
ዕብ. ምዕ. ፯÷ ቁ. ፩-፲፤
ራእ. ምዕ. ፫÷ ቁ. ፩-፲፤
ሐዋ. ምዕ. ፰÷ ቁ. ፳፮-፴፱፤

ምስባክ፡- መዝ. ፷፯÷ ቁ. ፴፩-፴፪፤

ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር፤
ነገሥተ ምድር፡ ሰብሕዎ ለእግዚአብሔር፤
ወዘምሩ ለአምላክነ።

ኢትዮጵያ፡ እጆቿን ወደእግዚአብሔር ትዘረጋለች፤
የምድር ገዢዎች፡ እግዚአብሔርን አመስግኑ፤
ለአምላካችን ዘምሩም።

ወንጌል፡- ማቴ. ምዕ. ፲፪÷ ቁ. ፵-፵፪።

## ፰ኛ፡ በደቡቡ ማዕዘን፤

# ስለቅድስት ድንግል ማርያም ልደት፤

ምንባብ፡-
ዕብ. ምዕ. ፱÷ ቁ. ፩-፫፤
ራእ. ምዕ. ፲፩÷ ቁ. ፲፫-፲፱፤
ሐዋ. ምዕ. ፩÷ ቁ. ፯-፲፬።

ምስባክ፡- መዝ. ፻፴፩÷ ቁ. ፲፫-፲፬፤

እስመ ኃረያ እግዚአብሔር ለጽዮን፤
ወኣብደራ፡ ከመ ትኩኖ ማኅደሮ፤
ዛቲ ይእቲ፡ ምዕራፍየ ለዓለም።

እግዚአብሔር ጽዮንን መርጧታልና፤
ማደሪያውም፡ ትኾነው ዘንድ ወዷታል፤
"ይህች፡ ለዘለዓለም ማረፊያዬ ናት!" አለ።

ወንጌል፡- ሉቃ. ምዕ. ፩÷ ቁ. ፳፮-፶፮።

## ፱ኛ፡ በምሥራቁ ማዕዘን፤

# ስለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ልደት፤

### የፍሬ ቅዳሴ፡

ምንባብ፡-
ገላ. ምዕ. ፬÷ ቁ. ፩-፯፤
፩ኛ ዮሐ. ምዕ. ፬÷ ቁ. ፩-፲፫፤
ሐዋ. ምዕ. ፲፫÷ ቁ. ፲፮-፳፫።

ምስባክ፡- መዝ. ፪÷ ቁ. ፯-፰፤

እግዚአብሔር ይቤለኒ ወልድየ አንተ፤
ወአነ ዮም ወለድኩከ፤
ሰኣል እምኔየ፡ እሁበከ አሕዛበ ለርስትከ።

እግዚአብሔር አለኝ፡ "አንተ ልጄ ነህ!"
እኔ፡ ዛሬ ወለድሁህ፤
ለምነኝ! አሕዛብን፡ ለርስትህ እሰጥሃለሁ።

ወንጌል፡- ሉቃ. ምዕ. ፪÷ ቁ. ፩-፳።

## የልደት ዝማሬ

**በኀል ሰከበ! በአጽርቅት ተጠብለለ!**

**ቤዛ ኵሉ ዓለም! ቤዛ ኵሉ ዓለም! ዮም ተወልደ!** *(፪ ጊዜያት)*

**ትርጉም**

**አምላክ፡ ሰው ኾኖ፡ ዓለሙ ኹሉ ሊያድን፡ ዛሬ ተወለደ!**

**በጨርቅ ተጠቅልሎ፡ በበረት ውስጥ ተኛ!**

---

**አንፈርዐፁ ሰብአ ሰገል!** *(፪ ጊዜያት)*

***አምኃሆሙ፡ አምጽኡ መድምመ።*** *(፪ ጊዜያት)*

---

**አማን፡ በአማን፡ አማን፡ በአማን!** *(፪ ጊዜያት)*

**መንክር ስብሓተ ልደቱ! መንክር ስብሓተ ልደቱ!** *(፪ ጊዜያት)*

**ትርጉም**

**እውነት በእውነት! እውነት በእውነት!**

**የክርስቶስ የልደቱ ገናንነት ዕፁብ ድንቅ ነው!**

---

## የምሥራች ሰላምታ

በዚህ በዓልና ከዚህ ቀን ጀምሮ፡ እስከ በዓለ ግዝረቱ፥ ከዚያም፡ እስከ በዓለ በአተ መቅደሱ ድረስ፡ ካህናትና ምእመናን፥ እርስ በርሳቸውም፡ የሚለዋወጡት የምሥራች ቃል፡-

ከመስከረም ፩ እስከ ፰ ቀን፡-

| | |
|---|---|
| *"ዮም ፍሥሓ ኮነ!"* | *"በእንተ ልደቱ ለክርስቶስ!"* |
| "ዛሬ ደስታ ኾነ!" | "የክርስቶስ የልደቱ በዓል ነውና!" |

ከመስከረም ፰ እስከጥቅምት ፱ ቀን፡-

| | |
|---|---|
| *"ዮም ፍሥሓ ኮነ!"* | *"በእንተ ግዝረቱ ለክርስቶስ!"* |
| "ዛሬ ደስታ ኾነ!" | "የክርስቶስ የግዝረቱ በዓል ነውና!" |

በጥቅምት ፲ ቀን፡-

| | |
|---|---|
| *"ዮም ፍሥሓ ኮነ!"* | *"በእንተ በአተ መቅደሱ ለክርስቶስ!"* |
| "ዛሬ ደስታ ኾነ!" | "ክርስቶስ፡ ወደቤተ መቅደስ የገባበት ቀን ነውና!" |

ይህ የደስታ መንፈስና መገለጫው፡ በፋሲካ ሥርዓት፡ እስከጥቅምት ፲ ቀን ይቀጥላል፡፡